


# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች

## “የራሳችን ጌታ” ከመሆን፥ “የጌታ ባሪያ” መሆን ይሻለናል

### በቃል የሚጠና፦ ሮሜ 12፥11

***“የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያዎች የሆኑ ጳውሎስና ጢሞቴዎስ፥ በፊልጵስዩስ ለሚኖሩ፥... (ፊልጵ. 1፥1)***

### 1 *መልዕክቱ የተጻፈበት ጊዜና ሁኔታ*

ሐዋርያው ጳውሎስ የጻፋቸውን ደብዳቤዎች በትክክል ለመረዳት፥ ለምን እንደተጻፈ፥ እንዲሁም ደብዳቤው በተጻፈበት ወቅት የነበረውን የጊዜ ሁኔታ ማወቅ በጣም ይጠቅማል። አብዛኛዎቹ በወቅቱ ለተነሱት አንዳንድ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የተጻፉ ናቸው። ለምሳሌ በቆሮንቶስ፥ በገላትያ፥ በፊሊጵስዩስ፥ በተሰሎንቄና እንዲሁም በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ፥ አንዳንድ ችግሮች ሲፈጠሩ፥ ለማጽናናት፥ ምክርም ሆነ ትዕዛዝ ለመስጠት የጻፋቸው ናቸው። ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎችም የተጻፈው መልዕክት ከዚያ የተለየ አልነበረም። መልዕክቶቹ ጳውሎስ በእጁ የጻፋቸው ሳይሆኑ፥ ለጸሐፊው እየነገረ ያጻፋቸው ደብዳቤዎች ናቸው። የደብዳቤው ባለቤት እርሱ እንደሆነ ማረጋገጫ እንዲሆን ብቻ መጨረሻው ላይ ፊርማውን ወይንም ስሙን ያኖር ነበር። *“እኔ ጳውሎስ ይህን ሰላምታ በገዛ እጄ ጽፌላችኋለሁ”* ያለው ለዚህ ነው (1 ቆሮ. 16፥21)። ደብዳቤዎቹን የጻፈው በአሁኑ ዘመን ያለነውን አማኞች እያሰበ ባይሆንም፥ ለእኛም ዘመን ወቅታዊ የሆኑ ትምህርቶችና መመሪያዎች እንደያዘ እናውቃለን። እኛን የማይመለከት ቢሆን ኖሮ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብና ማጥናት ባላስ ፈለገንም ነበር።

ጳውሎስ የፊልጵስዩስን መልዕክት የጻፈው ሮም ውስጥ ወህኒ ቤት በነበረበት ጊዜ ሲሆን፥ የጻፈበትም አራት ምክንያቶች ነበሩት፥

### 1 ከዚህ በፊት ስላደረጉለት ውለታ ለማመስገን ነው።

የፊልጵስዩስ ምዕመናን ጳውሎስን በብዙ አቅጣጫ ደግፈውታል *“... ከመጀመሪያው ቀን አንሥቶ እስከ አሁን የምሥራቹን ቃል በማወጅ የሥራዬ ተባባሪዎች ስለ ሆናችሁ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ”* ይላቸዋል (ፊልጵ. 1፥3)። ለምንሰጠው አገልግሎት ተባባሪ የሚሆኑትን ሰዎች ማግኘት ምን ያህል ትልቅ በረከት ነው?

### 2 የኤፖፍሮዲቶስን ሁኔታ ለመግለጽ ነው።

የፊልጵስዩስ አማኞች አንድ ጊዜ ከመካከላቸው *ኤፖፍሮዲቶስ* የተባለውን አማኝ ስጦታቸውን ለጳውሎስ እንዲያደርስና እንዲሁም ከእርሱ ጋር ቆይቶ በግል በሚያስፈልገው ነገር ሁሉ እንዲያግዘው ልከውት ነበር። ይሁን እንጂ፥ በጣም በመታመሙና እነርሱን በመናፈቁ ምክንያት ወደመጣበት ወደ ፊልጵስዩስ መልሶ ላከው። *ኤፖፍሮዲቶስ* ወደ እነርሱ ዘንድ የተመለሰው አገልግሎቱን ትቶ መሄዱ እንዳልሆነ እንዲያውቁት ደብዳቤ መጻፍ ነበረበት። *“እኔን እንዲረዳኝ ልካችሁት የነበረውን በጌታ ወንድማችን የሆነውን ኤፖፍሮዲቶስን ወደ እናንተ መላክ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፤ እርሱ ከእኔ ጋር የኢየሱስ ክርስቶስ ወታደር በመሆን በትጋት አብሮኝ ሲሠራ የቆየ ነው። እርሱን ወደ እናንተ የምልከውም ሁላችሁንም ለማየት በመናፈቁና መታመሙንም ስለ ሰማችሁ በሐዘን ስሜት በመዋጡ ነው”* አላቸው (ፊልጵ. 2፥25-26)።

### 3 በመከራቸው ሊያጽናናቸው ነው።

ጳውሎስ የፊልጵስዩስን መልዕክት የጻፈበት ሌላው ምክንያት፥ በዚያን ወቅት በመከራና በፈተና ውስጥ የነበሩትን የፊልጵስዩስን አማኞች *“አይዟችሁ! በርቱ”* በማለት ለማጽናናት ነበር (ፊልጵ. 1፥28-30።

### 4 ሕብረታቸውን እንዲጠብቁ ለመምከር ነው።

ጳውሎስ ይህን ደብዳቤ የጻፈበት ሌላው ምክንያት፥ የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን፥ ከውጪ በመጡ አንዳንድ አሰተኛ አስተማሪዎች፥ እንዲሁም ከውስጥ በተፈጠረ የእርስ በርስ ግጭት ምክንያት ሳይታወኩ አንድነታቸውንና ፍቅራቸውን ተግተው እንዲጠብቁ ለመምከርና ለማሳሰብ ነበር።

## 2 ጳውሎስ ራሱን የክርስቶስ ባሪያ አድርጎ ያስተዋውቃል

***"የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያዎች የሆኑ ጳውሎስና ጢሞቴዎስ፥ በፊልጵስዩስ ለሚኖሩ፥... (ፊልጵ. 1፥1)*** ይላል። ጳውሎስ ከጻፋቸው ደብዳቤዎች መካከል ለፊልጵስዩስ አማኞች የጻፈው ደብዳቤ፥ መግቢያው የተለየ እንደሆነ እናያለን። ጳውሎስ በአብዛኛዎቹ ላይ መልዕክቱን የሚጀምረው፥ ***"...የክርስቶስ ሐዋርያ የሆነ"*** በማለት **"ሐዋርያነቱን"** በመግለጽ ነው። ይህን የሚያደርገው፥ መልዕክቱን ለመጻፍ ሙሉ ስልጣን እንዳለው፥ እንዲሁም መልዕክቱ የተጻፈላቸው ክፍሎች መልዕክቱን የማንበብና የመታዘዝ ግዴታ እንዳለባቸው ለመግለጽ ነው። ለፊልጵስዩስ አማኞች በጻፈው መልዕክት ላይ ግን ***"ሐዋርያነቱን"*** አይገልጽም። ጳውሎስ ከእነርሱ ጋር የተቀራረበ ግንኙነት ስለነበረው፥ ማንነቱን ስለሚያውቁ፥ የሚልከው መልዕክት ተሰሚና ተቀባይነት እንዳለው ስለሚያውቅ ነው።

***"የክርስቶስ ባሪያ"*** የሚለውን ማዕረጉን ግን የሚኮራበት እንጂ የሚያፍርበት ስላልሆነ ከመግለጽ ወደ ኋላ አላለም። ጳውሎስ ራሱን ***"ባያ"*** ብሎ ሲጠራ፥ ዝም ብሎ ሳይሆን፥ በደረጃው ***"ባሪያ"*** ከአሽከር ያነሰ እንደሆነ አውቆ ነው። ***"አሽከር"*** ቀጣሪው ካላስደሰተው፥ በቂ ደሞዝ ካልከፈለው፥ ኑሮው እንደሚፈልገው ካልተመቻቸለት፥ በፈለገበት ጊዜና ሥራውን ትቶ የመሄድ መብት አለው። ***"ባሪያ"*** ግን ያንን ዓይነት መብት የለውም። ***"ባሪያ"*** የራሱ ሳይሆን፥ የጌታው ንብረት ነው። ደስ ካላለው፥ ትቶ የመሄድ መብት የለውም። እስከ ሕይወቱ መጨረሻ ድረስ፥ የጌታው አገልጋይ ወይንም ንብረት ሆኖ ይቀያል።

## 3 ጳውሎስ ራሱን *"የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ"* ብሎ ሲጠራ፥ ምን ማለቱ ይሆን?

ጳውሎስ ራሱን ***"የክርስቶስ ባሪያ"*** ብሎ ሲጠራ፥

(ሀ) ***"እኔ የራሴ አይደለሁም፤*** ሙሉ በሙሉ የጌታ ነኝ፤ የራሴ የሆነ ምርጫ የለኝም፤ ያለኝን የመምረጥ መብት ለጌታ በፈቃዴ ትቻለሁ። እኔ የጌታዬ ንብረት ወይንም ዕቃ ስለሆንኩ፥ በሕይወቴ የፈለገውን ለማድረግ ይችላል" ማለቱ ነው። ጳውሎስ ***"የክርስቶስ ባሪያ"*** ብሎ ራሱን የሚጠራው ክርስቶስ በጣም እንደወደደውና ውድ በሆነው በደሙ እንደገዛው ስለሚያምን ነው። ጳውሎስ ***"በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም..."*** ያለው ለዚህ ነው (1 ቆሮ. 6፥20)። እኔና እናንተስ የማን ነን? ብዙዎቻችን የማንም ሳንሆን የራሳችን ነን። ማንም አይገዛንም። የፈቀድነውን፥ ደስ ያለንን እናደርጋለን። ከራሳችን ጋር በጣም የተያያዝን ነን። ይሁን እንጂ፥ መንፈሳዊ ችግራችን፥ አሸናፊ የክርስትና ሕይወት እንዳንኖር እንቅፋት የሆነብን፥ ከራሳችን ተላቅን፥ በውድ ዋጋ ከገዛን ጌታ ጋር መጣበቅ፥ እንዲሁም ራሳችንን ሙሉ በሙሉ መስጠት ስለሚያቅተን ነው።

(ለ) *ጳውሎስ ራሱን "የክርስቶስ ባሪያ"* ብሎ የጠራበት ሌላው ምክንያት፥ ***ለክርስቶስ ያለውን ፍጹም የሆነ ታዛዥነቱን መግለጹ ነው።*** ባሪያ የራሱ ፈቃድ የለውም። ጌታውን "እምቢ!" ማለት አይችልም። "ተነስ!" ሲባል ይነሳል፥ "ተቀመጥ!" ሲባል ይቀመጣል፥ "ሂድ" ሲባል ይሄዳል። የራሱ የሆነ ምርጫ የለውም፤ ምርጫው የጌታው ነው። ጳውሎስም እንደ ባሪያ የራሱን ፈቃድ ትቶ ኢየሱስ ክርስቶስን ብቻ እንደሚታዘዝ መግለጹ ነው። ብዙዎቻችን "የጌታ ነን" እንላለን። ይሁን እንጂ፥ ሁልጊዜ አንታዘዘውም። የምንታዘዘው እኛን ደስ ሲለን፥ ቀላል የሚመስለንን እየመረጥን ብቻ ነው። ***"የክርስቶስ ኢየሱስ ባሪያ"*** ከሆንን፥ የራሳችንን ፈቃድና ምርጫ መተው አለብን።

## 4 ከዚህ ክፍል የምናገኘው ትምህርት ምንድነው?


(ሀ) ***እኛ የራሳችን አይደለንም።*** ለሕይወታችን መሳካት ወሳኙ፥ የሕይወታችን ባለቤት ማን መሆኑን ማወቁ ነው። ሕይወቱ ፍሬያማ እንዲሆን የሚፈልግ ማንኛውም አማኝ፥ ከራሱ የተላቀቀ፥ ወይንም ሕይወትን ለሰጠ ጌታ መልሶ መስጠት የቻለ እንደሆነ ብቻ ነው።

(ለ) ***"የራሳችን ጌቶች" ከሆንን፥ ራሳችንን እንጎዳለን።*** "የራሳችን ጌቶች" በመሆናችን ልክ የሆንን ይምሰለን እንጂ፥ መጨረሻችን ያማረ አይሆንልንም። አንድ ጊዜ አንድ መንገድ የጠፋበት ሰው፥ መንገድ ላይ ይጫወት የነበረውን ትንሽ ልጅ፥ የከተማውን ስም ጠርቶ "እንዲህ የሚባለው ከተማ ምን ያህል ይርቃል?" ብሎ ጠየቀ። ልጁም ሲመልስ፥ "አሁን የያዝከውን አቅጣጫ ይዘህ ቀጥ ብለህ ከሄድክ፥ ከሃያ አምስ ሺ ማይልስ በላይ ይርቃል። ፊትህን አዙረህ በመጣህበት መንገድ ከሄድክ ግን፥ 3 ማይልስ (4.8 ኪሎ ሜትር) ብቻ ይርቃል" አለው። በራሳችን አሳብና ምርጫ ሕይወታችንን የምንመራ ከሆነ፥ ያለ ትክክለኛ መሪ ነንና መንገዳችንን ስተን የትም እንጠፋለን።

(ሐ) ***ባሪያ ራሱን ለጌታው እንደሚያስገዛው፥ ለጌታ ራሳችንን ብናስገዛ እንጠቀማለን እንጂ አንጎዳም።*** "የጌታ ባሪያ" በመሆን ፈንታ "የራሳችን ጌታ" መሆንን ከመረጥን፥ አሁን ያለንበት ሕይወት የማያምር መሆኑ ብቻ ሳይሆን መጨረሻችንም የከፋ ይሆናል። ስለሆነም፥ ጌታን "ሕይወቴ ይኸውልህ! የፈለግኸውን አድርግ" ብለን ራሳችንን ለእርሱ እንስጠው። የራሳችን ባሪያዎች ከመሆን፥ የጌታ ባሪያዎች መሆን የበለጠ ውጤት እንደሚያስገኝ እንወቅ።

---

**በውኑ ቃሌ እንደ እሳት**



**ድንጋዩንም እንደሚያደቅቅ መዶሻ አይደለችምን? ይላል እግዚአብሔር።**

**(ኤርምያስ 23፥29)**




## ሀ የመልእክቱን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት

① ጳውሎስ የፊልጵስዩስን መጽሐፍ የጻፈው የት ሆኖ ነው?

② ጳውሎስ የፊልጵስዩስን መልዕክት የጻፈበትን አራት ምክንያቶች ዘርዝር፥

ሀ.

ለ.

ሐ.

መ.

③ ጳውሎስ ይህን መልዕክት የላከው በማን በኩል ነበር? (ፊልጵ. 2፥25-26)

④ ጳውሎስ ራሱን ለፊልጵስዩስ አማኞች ያስተዋወቀው እንዴት ብሎ ነው? (ፊልጵ. 1፥1)

⑤ ጳውሎስ ከጻፋቸው ደብዳቤዎች መካከል ለፊልጵስዩስ አማኞች የጻፈው ደብዳቤ መግቢያው የሚለየው እንዴት ነው?

⑥ በሌሎቹ መልዕክቶቹ ውስጥ "ሐዋርያነቱን" የሚገልጸው ለምንድነው?

⑦ በፊልጵስዩስ መልዕክቱ ላይ "ሐዋርያ" ብሎ ራሱን ያላስ ተዋወቀው ለምንድነው?

⑧ በአሽከርና በባሪያ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

⑨ ጳውሎስ ራሱን "የክርስቶስ ባሪያ ያለበት ምክንያት ምንድነው?

ሀ.

ለ.

⑩ ክፍ የማለት ምስጢሩ ምንድነው?

## ለ በዚህ ክፍል ውስጥ ያገኘነውን ትምሕርት በግል ሕይወታችን ለመለማመድ...

① በሕይወትህ (በሕይወትሽ) መንፈሳዊም ሆነ ሥጋዊ ድጋፍ ያደረጉልህ (ያደረጉልሽ) ሰዎች አሉ? ካሉ ስማቸውንና ያደረጉልህን (ያደረጉልሽን) በጎ ነገር ጻፍ (ጻፊ)።

② ውለታቸውን በማስታወስ ያደረግኸው (ያደረግሽው) ነገር ምንድነው?

③ ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ አማኞች ስላደረጉለት በጎ ነገር የምስጋና ደብዳቤ እንደጻፈላቸው ተመልክተናል። አንተስ (አንቺስ) ምንም ያህል ጊዜው የቆየ ቢሆንም የምስጋና ደብዳቤ ብትጽፍላቸውስ? (ብትጽፊላቸውስ)? ይህን ለማ ድረግ ጌታ ይርዳችሁ።


④ ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ አማኞች ደብዳቤ ለመጻፍ የተነሳ በት ሌላው ምክንያት በመከራ ውስጥ ያልፉ ስለነበረ፥ በመከራቸው ብርቱዎች እንዲሆኑ ለማጽናናት እንደነበረ

ተመልክተናል (ፊልጵ. 1፥28-30)። በአሁኑ ጊዜ የምታውቃቸው (የምታውቂያቸው) በመከራ (በችግር) ውስጥ በማለፍ ላይ ያሉ ክርስቲያኖች አሉ? የሚያጽናና ደብዳቤ ብትጽፍላቸው (ብትጽፊላቸው) ትልቅ አገልግሎት መስጠት አይመስልህም? (አይመስልሽም?)

⑤ ጳውሎስ ራሱን "የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ" ብሎ የጠራበት አንደኛው ምክንያት ፍጹም የሆነ ታዛዥነቱን ለመግለጽ ነው። አንተስ (አንቺስ) ጌታን ያልታዘዝክባቸው (ያልታዘዝሽባቸው) ነገሮች ወይንም ሁኔታዎች የትኞቹ ናቸው?


⑥ ራስህን (ራስሽን) ዝቅ ማድረድ የተቸገርክበት (የተቸገርሽበት) ሁኔታዎች ምንድናቸው?

⑦ "ትህትናን በሕይወቴ ለመለማመድ ይህንንና ያንን ለማድረግ ወስኛለሁ" የምትላቸው (የምትያቸው) ነገሮች አሉ? ካሉ፥ ዘርዝረህ (ዘርዝረሽ) ጻፋቸው (ጻፊያቸው)።



"...የመዳንን ራስ ቁር የመንፈስን ሰይፍ ያዙ፥ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።..."

(ኤፌሶን 6፥17)



የትምሕርቱ አዘጋጅ
መለሰ ወጉ

# ስንቅና ትጥቅ

በኢትዮጵያውያን የወንጌል አገልግሎት ተዘጋጅቶ፥ በየሁለት ሳምንቱ እየታተመ የሚወጣ ግላዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ነው።

**Ethiopian Outreach Ministry**
**P.O.Box 2241**
**York, PA 17405**
**U.S.A.**
**Phone/Fax: (717)846-2041**
**E-Mail: eomusa@aol.com**
**Internet Address:**
**www.ethiopianoutreach.com**

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን
አድራሻ